


CamScanner

፩ አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱ ስም ሰኔ ፲፮ ቀን የሚነበብ የኪዳነ ምሕረት ድርሳን ይህ ነው ::ልመናዋ ክብሯ ለዘለዓለሙ ከሁላችን ጋር ይደርብን::

፪ ልጄ ወዳጄ ሁሉን ሀብት ሰጠኸኝ፡ በምድር ላይም

ማደሪያን መረጥኸኝ፡ በሲኦል ያሉትን ነፍሳት አውጥተህ

ፈቃዴን ትፈጽምልኝ ዘንድ እወዳለሁኝ፡

ጩኸታቸውን ሰምቻለሁኝና::

፫ እመቤታችን ለጌታ ይህን በነገረችው ጊዜ ስለእናቱ ማርያም ቸርነት ደስ ተሰኝ፡ ያን ጊዜም ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማርያምን ስለአንቺ ፍጥረቱን እምራለሁ አላት::

፬ ሐዋርያት ለፍጥረቱ ሁሉ ያለሽን ቸርነት አይተው መታሰቢያሽን በዓለሙ ሁሉ ያስተምራሉ፡ ሁሉም እያንዳንዱ የዓለም መድኀኒት ናት እያሉ እንዲያመሰግኑ::

፭ ከዚህ በኋላ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እናቱ ቃል ኪዳን በመከራ ቦታ በጨለማ ውስጥ ያሉ ነፍሳት እንዲወጡ አዘዘ፡ በስሜ አምነው ከተጠመቁት አንዲት ነፍስ ሳትቀር ሁላቸውን አወጣቸዋለሁኝ አለ:: በመከራ ቦታ በሲኦል ውስጥ ሆነው በሥቃይ የሚጮሁት ሁሉ ይወጣሉ፡ የእኔ ፍርድ፣የአባቴ ፍርድ የመንፈስ ቅዱስም ፍርድ ስለእናቴ ስለ እመቤታችን ልመና ነፍሳትን ሁሉ ታድናቸዋለች:: ከእንግዲህስ ወዲህ በገሃነም ሥቃይ አይኖሩም እንደመላእክት በእግዚአብሔር ቤት በተድላ በደስታ ይኖራሉ እንጂ::

፮ ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሠራዒ ቄስ፣ አስጢፋኖስ ዲያቆን፣ ጴጥሮስ ተራዳኢ ቄስ ሆነው አምላክን የወለደች የእመቤታችን ሥጋ ባለበት ቦታ ቀደሱ።

፯ ደቀ መዛሙርቱም ሁሉ በዙሪያው ከብሩ በእጃቸው ኅብስቱን በመፈተት ሁላቸው ከጌታ ጋር እንደ አንድ አድ ሆነዋል።

፰ ካህናት እንደሚያደርጉት በቅዳሴና በቍርባን ሥርዐት አግዘእታውን ሲጨርስ ደቀመዛሙርቱን ስጋውን ደሙን አቀበላቸው። በዚህ ቦታ ከመላእክት ጋር አንድ ሆኑ።

፱ እመቤታችንም በልጇ ወዳጇ እጅ ስጋውን ደሙን ተቀበለች።

፲ እመቤታችን ከቆረበች በኋላ ጌታ ክርስቶስ ተናገራት እናቴ ማርያም ሆይ ዛሬ ለፍልሰትሽ፣ለዕርገትሽ መታሰቢያ የሆነው ይህ ቁርባን የተዘጋጀው ልጆችሽ ሐዋርያት መታሰቢያሽን በዓለሙ ሁሉ ያስተምሩ ዘንድ ነው እያለ አረጋጋት።

፲፩ በዕረፍትሽ ቀን ወደሰማይ ባረግሽበት ዕለት ይህውም ነሐሴ ፲፮ ቀን መታሰቢያሽን የሚያደርገውን ለሥጋ ወደሙ የተዘጋጀውን ሰው ሁሉ በመንግስቴ ያሉ ማኅበረ በኵር የተባሉ የእነ አቤልን መሥዋዕት እንደተቀበልሁ መሥዋዕቱን እቀበለዋለሁ።

የቃል ኪዳንሽን መጽሐፍ የሚጽፈውን ሁሉ እኔ ስሙን በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ እጽፈዋለሁ፡ ለእርሱም ለልጆቹም በመንግሥተ ሰማያት መኖሪያ ቤትን እሰጠዋለሁ።

የተራቆተውን፣ በስምሽ ያለበሰውን እኔ የብርሃን ልብስ አልብሼ በብርሃን ቤት አኖረዋለሁ፡ ስለ ስምሽ መሥዋዕት ያቀረበውን ዕጣንም የሰጠውን ሰው ለዘለዓለሙ ባለሟልነትን እሰጠዋለሁ።

እመቤታችንም ልጇ ወዳጇ ሆይ ስለ በጎ ምግባራት በዓለሙ ሁሉ ያስተምሩ ዘንድ ለደቀ መዛሙርትህ ብዙ ጊዜ ስታስተምራቸው ሰማሁኝ አለች፡ ለዓለም የሚሆን የእግዚአብሔር ሕግ ነውና።

አሁንም አንተን በዓይናቸው አዩ፤በእጃቸው ዳሰሱ፤ ትምህርትህን በጆሮአቸው ሰሙ፤ከዚህም የሚበልጥ የለም።

ወደ ሰማያት ባረግሁበት ቀን በእጅህ በተቀበልሁት የቁርባን ምስጢር አንድነት ታላቅ ምስጢርን ገልፅህላቸዋልና።

ድኅነትን የሚሆን ነገርንም የገለፀህላቸው ትንሣኤም ሕይወትም አንተ ነህና።

እመቤታችን ልጇ ወዳጇ ይህን በተናገረች ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለች መቅረዝ አበራች፡

፲፰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በእመቤታችን ቅዳሴ ጊዜ መላእክት ከሐዋርያት ጋር እንዲሳሉ አዘዛቸው።

፲፱ እኔም ይህን ድንቅ ነገር ሳስብ ደቀመዛሙርቱ በብርሃናዊት ደመና ውስጥ ተሠወሩ፡ መላእክት ወዴት ቦታ እንደወሰዷቸውም አላወቅሁም።

፳ እኔ አብርኮርስም የቤተክርስቲያን ሥርዐቶቿን አይቼ ካወቅሁኝ በኋላ ወደ እስያ ሄድኩኝ፡ መምህሬ ዮሐንስ አስድሞ እንደነገረኝ እመቤታችን ማርያምን አየኋት።

፳፩ እነሆ ዮሐንስም ፊቱ በጸዳለ ብርሃን ተከቦ ከእመቤታችን ጋር ቆሞ ነበር።

፳፪ ዳግመኛ ደቀመዛሙርቱ የንጽሕት እመቤታችን ሥጋዋ ካለበት በዕርገቷ ጊዜ ቢሰበሰቡ እስከ ነገ ድረስ ጠብቃቸው እወቃቸው አለኝ፡

እርሷ ሰማይና ምድርን የፈጠረ እግዚአብሔር አብ በባሕርይ የወለደው የብርሃን ማደርያ ናትና፡ እርሱ ቅድመ ዓለም የነበረ ሲሆን ማደርያው ትሆን ዘንድ ከመረጣት ድንግል ማርያም ሰው ሆነ፡ ልመናዋ ክብሯ ለዘለዓለሙ ከሁላችን ጋር ይደርብን አሜን።

፩ ልመናዋ ክብሯ ለዘለዓለሙ ከሁላችን ጋር ይደርብንና የምሕረት እናት የእመቤታችን ተአምር ይህ ነው

፪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ማርያምን እናቴ ሆይ በማህፀንሽ ያደርሁብሽ አዲስ ምድር የተባልሽ አንቺ ነሽ አላት፡ በመስቀል ተሰቅሎ ሳለ ያዘነችውን ልቅሶ አሰበ፡፡

፫ እንደዚህም መላእክት ሁሉ የመለኮት ማደርያ ናት እያሉ ማርያምን ያመሰግኗታል፡፡

፬ ዳግመኛም በመከራዩና በምሞትበት ዕለት ከመስቀሉ እግር መቆምን መረጠች አለ፡ ሠረገላ የተባለች ማርያም እናቴ በቀራንዮ ሳለሁ በቀኜ ቆማ በእኔ ላይ የደረሰውን መከራ አየች፡፡

፭ እንደዚሁም ዜና ዕረፍቷንና በዐሏን እንድናስብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳዘዘ፡፡

፮ እኔም አባታችሁ አባ ጊዮርጊስ ጌታ ክርስቶስ ከተነሣ በኋላ ሕጉን ለማስተማር ፍለጋውን ተከተልሁ፡ ጥር ፳፩ ቀን ያረፈችበት ነሐሴ ፲፮ በታላቅ ክብር ወደሰማይ ያረገችበት ቀን እንደሆነ ፡

፯ እነሆ ከመጻሕፍት አግኝቼ ጻፍሁላችሁ፡ አይሁድ ሥጋዋ በጌቴሴማኒ በመቃብር ውስጥ እንዴት ተገኘ? አልተገኘም እንዳይሉ፡፡

፰ የእመቤታችን ሥጋ የተቀበረባትን ምድርም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባረካት።

፱ ቤተመቅደሷ በዐረባውያን መካከል ሚልጥያኖስ በሚባል ቦታ ታነፀ። እሊህም ስለእመቤታችን ቅድስት ማርያም ሥጋ ምትሐት ነው የሚሉ ናቸው።

፲ ወደሰማይ እንዳላረገች የሚናገሩ ናቸው፡ ልብ የሌላቸው አይሁድ ውሾችን ወደ እመቤታችን ሥጋና ወደ ሐዋርያት በሰደዷቸው ጊዜ ሊያገኙ ስላልቻሉ ምትሀት ነው አሉ።

፲፩ እግዚአብሔር ግን የሥጋዋን ቦታ አዘጋጀ።

፲፪ ወንድሞቼ ስለዚህ በድንግልና ሥጋ በድንግልና ኅሊና ኅትምት የምትሆን የእመቤታችንን መታሰቢያ እናክብር።

፲፫ አባ ጊዮርጊስም ዕርገቷን ውዳሴ ድንግል በሚባል መጽሐፍ ጽፏል። ልመናዋ ክብሯ ለዘለዓለሙ ከሁላችን ጋር ይደርብን አሜን።